# ምን ይጠብቃሉ፡ የግዛቱ የኮቪድ-19 የክትባት ጣቢያ ጉብኝት ላይ የተጻፈ ጽሁፍ

*[ጣፋጭ ሙዚቃ]*

[የመኪና ማቆሚያ ተቀባይ] እንዴት አደራችሁ! ዛሬ ቀጠሮ አልዎት?

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] አዎ፣ ቀጠሮ አለን።

[የመኪና ማቆሚያ ተቀባይ] አዎ፣ ቀጠሮ አልዎት፣ መልካም። የሁለታችሁም እድሜ ከ 18 አመት በላይ ነው?

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] አዎ፣ እድሜያችን ከ 18 አመት በላይ ነው።

[የመኪና ማቆሚያ ተቀባይ] እሺ። የአካል ጉዳት የመንቀሳቀስ ችግሮች ወይም የመራመድ ችግር አለባችሁ?

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] አይ

[የመኪና ማቆሚያ ተቀባይ] እሺ። ቀጥሎ የሚሆነው በቀጥታ ወደ ፊት መሄድ ነዉ። ቡርትካናማ ልብስ ያደረጉት ሰዎች የት መኪና እንደሚያቆሙ ያሳይዎታል። ካቆሙ በኋላ፣ ወደ ትልቁ ድንኳን ይሄዳሉ። ደስ የሚል ቀን ይሁንልዎ።

*[ጣፋጭ ሙዚቃ]*

[የውጪ ተቀባይ] አሁን ያደረጉት የፊት መሸፈኛ ላይ ይህንን ያድርጉ። ባር ኮድዎን ያዘጋጁ። ድንኳን ውስጥበቀኝዎ በኩል ባለው ።

*[ጣፋጭ ሙዚቃ]*

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] ሁሉም የግዛቱ የክትባት ጣቢያዎች የቋንቋ እገዛ አላቸው።

[የውስጥ ሰራተኛ] እንዴት ኖት እማማ? የቀጠሮዎን ባር ኮድ መመልከት እችላለሁ? እሺ እባክዎ በዚህ መንገድ ይሂዱ። እዛ ሲደርሱ ይንከባከብዎታል እንዲሁም የሚሄዱበትን ጠረጴዛ ይሰይምዎታል።

*[ጣፋጭ ሙዚቃ]*

የመስመር ሰራተኛእንዴት ናችሁ፣ ዝግጁ ናችሁ፣ ደስተኛ ናችሁ? እሺ፣ ይህ በጣም ቀላል ነው የሚሆነው። ባር ኮድዎ ከዚህ በኋላ አያስፈልግዎትም፤ ዝም ብለን እንቀጥላለን እናም በስልክ ቁጥርዎ እናወጣዋለን። ስለዚህ ዝግጁ ሲሆኑ ወደ ተራ ቁጥር አንድ እንልክዎታለን።

*[ጣፋጭ ሙዚቃ]*

[የምዝገባ ሰራተኛ] ሰላም፣ እንዴት አደራችሁ። የተመዘገቡበትን ስልክ ቁጥር ማግኘት እችላለው? ስምዎን እና የልደት ቀንዎን እንዲያረጋግጡ ማድረግ እችላለው? ይህ የመጀመሪያ የክትባት መጠንዎ ነው?

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] አዎ

[የምዝገባ ሰራተኛ] ዛሬ የኮቪድ ምልክቶች እየተሰማዎት ነው?

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] አይ

[የምዝገባ ሰራተኛ] ባለፉት 14 ቀናት ኮቪድ ለያዘው ማንኛውም ሰው ተጋላጭ ነበሩ?

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] አይ

[የምዝገባ ሰራተኛ] መውሰድ የሚፈልጉ ከሆነ እዚህ ጋር ስለ ክትባቱ የተወሰኑ መረጃዎች አሉ እናም እሷ የት እንደሚሄዱ ታሳይዎታለች።

[የውስጥ ሰራተኛ] ሰላም እማማ እንዴት አደሩ። እባክዎ ይከተሉኝ።

*[ጣፋጭ ሙዚቃ]*

[የክትባት ሰራተኛ] እባክዎን ሙሉ ስምዎን እና የልደት ቀንዎን እንዲያረጋግጡ ማድረግ እችላለው? በፍጥነት የተወሰኑ ጥያቄዎችን እጠይቅዎታለው። ስሜ ሺያን ስኪነር ይባላል፤ ዛሬ ክትባትዎን የምሰጥዎት እኔ ነኝ። ባለፉት 14 ቀናት ክትባት ወስደዋል?

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] አይ

[የክትባት ሰራተኛ] የጉንፋን ወይም የኢንፍሉዌንዛ የሚመስሉ ምልክቶች አልዎት?

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] አይ

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] ስለ ማንኛውም አለርጂዎች ወይም ስላለፉ የክትባት የአለርጂ ግብረ መልሶች ይጠየቃሉ።

[የክትባት ሰራተኛ] ከዚህ በኋላ ማንኛውም ጥያቄዎች አልዎት?

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] ክትባቱ ያማል?

[የክትባት ሰራተኛ] ምናልባት ምንም ነገር አይሰማዎትም፤ ከተሰማዎት ደግሞ ከቁንጥጫ ያነሰ ስሜት ነው የሚሆነው። መጀመር ይችላሉ እናም የግራ ትከሻዎን ይግለጡልኝ።

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] ሳያስቡት በፍጥነት ይጨርሳሉ።

[የክትባት ሰራተኛ] ስለዚህ ይህ የእርስዎ የክትባት ካርድ ነው። ቀጥለው ማድረግ ያለበት እዚህ ላይ መረጃዎን ይሞላሉ እናም ለሁለተኛ የክትባት ዶዝ ሲመጡ ይህንን ከእርስዎ ጋር ይዘው መምጣትዎን ያረጋግጡ። ይህ የእርስዎ ሁለተኛ የክትባት ዶዝ የሚመዘገብበት ነው። አሁን የሚሄዱ ይሆናል -- ከጥቂሩ መጋረጃ ጀርባ ወዳለው የምልከታ ቦታ ይሂዱ። ስለዚህ ለ 15 ደቂቃ ያህል እዛ ይጠብቃሉ ከዚያም በኋላ መሄድ ይችላሉ።

*[ጣፋጭ ሙዚቃ]*

[የምልከታ ሰራተኛ] ሰላም፣ እንዴት አደራችሁ! እባክዎ በዚህ በኩል ካሉት ወንበሮች በአንዱ ይቀመጡ። ለራስዎ 15 ደቂቃ ሰአት ይይዛሉ። ጥያቄዎች፣ ስጋቶች ካልዎት እጅዎን ከፍ ያድርጉ። እናም 15 ደቂቃውን ሲጨርሱ፣ መውጫዎ በስተግራ በኩል አለ።

*[ጣፋጭ ሙዚቃ]*

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] ከ 15 ደቂቃ በኋላ።

*[ጣፋጭ ሙዚቃ]*

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] በራስ ፎቶ መነሻ ጣቢያው የራስ ፎቶ ይነሱ። #RollUpYourSleevesMN ብለው ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ይለጥፉ።

*[ጣፋጭ ሙዚቃ]*

[የማያ ገጽ ጽሁፍ] የኮቪድ-19 ክትባት ቀጠሮ ዛሬውኑ ይያዙ! Vaccineconnector.mn.gov ወይም 833-431-2053 ላይ ይደውሉ (ከሰኞ-አርብ 9 a.m. – 7 p.m.፣ ቅዳሜ 10 a.m. – 6 p.m.)

*[ጣፋጭ ሙዚቃ]*

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

5/12/21 (Amharic)

*ይህን መረጃ በተለየ ቅርጸት ለማግኘት፣ በሚከተለው ይደውሉ፡ 651-201-4989*